# ክቡር ኢንጂነር ኃይሉ ሻውል ሴቶችና ወጣቶችን አወያዩ፡፡

ክቡር ኢንጂነር ኃይሉ ሻውል የቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ፓርቲ



ፕሬዚዳንት የፓርቲውን የወቅቱን ተግባራዊ እንቅስቃሴና በመጭው ጊዜያት ሕዝባዊ አድማሱን በበለጠ ለማስፋት መከናወን ስለሚኖርባቸው ተግባራት በማስመልከት ሴቶችንና ወጣቶችን ሰኔ 8 ቀን 2000 ዓ.ም በፓርቲው ጽህፈት ቤት ተገኝተው አወያዩ፡፡

ለዘጠኝ ወራት በውጭ ሀገር ቆይተው ከተመለሱ በኋላ ሴቶችንና ወጣቶችን እንዲያወያዩ ለመጀመሪያ ጊዜ በተዘጋጀው በዚሁ መድርክ ላይ ክቡር ኢንጂነር ኃይሉ ሻውል ባሰሙት ንግግር ህዝቡ ሲጠናከር አገዛዙ ጭቆናውን በህዝብ ላይ እንደሚያጠናክር አስረድተው በዚህም መሰረት በዙ የፓርቲው ደጋፊዎች ልጆቻቸው እንደተገደሉባቸው፤ ለእስራት እንደተዳረጉባቸው እንዲሁም ከቤት ንብረታቸው እንደተፈናቀሉባቸው አስታውሰዋል፡፡ ሕዝቡን በማስፈራራት በጉልበት ዝም ማሰኘት ይቻላል ነገር ግን በዚህ አካሄድ መውደድን ማትረፍ ፈጽሞ እንደማይቻል ተናግረዋል፡፡

‹‹ተስፋ የሌለው የሞተ ሰው ብቻ ነው፤ እኛ ግን ስላልሞትን ተስፋ አለን ›› ያሉት ክቡር ኢንጂነር ኃይሉ ሻውል አያይዘውም ‹‹እስቲ እዚያ ጋ ያለችውን ያቺን ህፃን ልጅ ተመልከቷት ቤተ ሰቦቿ ተስፋ ስላደረጉ ነው ወደዚህ ስብሰባ ይዘዋት የመጡት፡፡›› ፕሬዚዳንቱ በመጨረሻም ‹‹ብዙና ከባድ ሥራዎች ይጠብቁናል፤

ከእናንተ የአንጎል ጥንካሬና አካባቢያችሁን የማወቅ፣ ከእኛ ደግሞ የምንሄድበትን አቅጣጫ የማሳየት፣ እንዲህ ከተጓዝን እናሸንፋለን›› ብለዋል፡፡

ቀደም ሲልም ወ/ሮ አለማየሁ ሞገድ የቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ፓርቲ



የአዲስ አበባ የሴቶች ኮሚቴ ኃላፊ ባሰሙት ንግግር ይህ ፓርቲ እዚህ እንዲደርስ የወደቁ ወገኖቻችን አርማ አንስተን መታገል አለብን ብለን ጊዜያዊ አደራጅ የሴቶች ኮሜቴ አቋቁመን እንቅስቃሴ ጀመርን በማለት ሴቶችን በማደራጀት በኩል የተደረጉት ክንዋኔዎች አስመልክው አብራርተዋል፡፡ ወደፊትም የፓርቲውን ድርጅታዊ መዋቅር በመከተል በማደራጀቱ ሂደት የበለጠ ለመሥራት ዝግጁ መሆናቸውን አረጋግጠዋል፡፡



እንዲሁም ወጣት ጌታነህ ዓለም የአዲስ አበባ ወጣቶች ኮሚቴ አስተባባሪ ባሰሙት ንግግር ቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ፓርቲ የረጅም ጊዜ የነፃነትና የአንድነት ታጋዮች የትግል ውጤት መሆኑን ገልጸዋል፡፡ በቅንጅት ፓርቲ መሪነት

የኢትዮጵያን ትንሳኤ ከመቸውም ጊዜ በበለጠ ለማየት እንደሚፈልጉና በሰላማዊ ትግሉም ወጣቱ በዓላማ ጽናትና በቁርጠኝነት የበኩሉን አስተዋጽኦ ሁሉ ለማድረግ ዝግጁ እንደሆነ ገልጸዋል።

በዕለቱ ተሳታፊዎች ልዩ ልዩ ጥያቄዎች ተነስተው ክቡር ኢንጂነር ኃይሉ ሻውል ተገቢውን መልሶች ሰጥተዋል። በዚሁ ውይይት ከሁለት መቶ በላይ ሰዎች ተሳታፊ ሆነዋል።